"ያልተፈታ ህልም"

ክፍል 1

✍ በሂክማ ጀማል

፡

፡

እኔም እንደ አብዛኛው ሰው ተፈጥሮን አደንቃለሁ ዛሬ በጠዋት ነው የነቃሁት ቀኑ ደስ ይላል ፀሀይ በትንሹ እንደመውጣት እያለች ነው እኔም በትንሹ የወጣችውን ፀሀይ ለመሞቅ ፀሀይዋ ወደ አለችበት አቅጣጫ በእንጨት ከተሰራው ትንሹ ወንበር ላይ ተቀምጬ ፀሀይ እየሞኩ ነው። የተወሰነ እንደሞኩኝ ሰውነቴ መነቃቃት ሲጀምር ከ እቤት በኩል በተደጋጋሚ ሰሚር .... ሰሚር እያለች በምትጠራኝ በ እማዬ ድምፅ ነበር ከተቀመጥኩበት የተነሳሁት። ወደ እቤት ስገባ እማዬ ቁርስ ሰርታ ጨርሳ አቀራርባ ነበር አንድበላ የጠራችኝ በዛች በደሳሳ ጎጆ ውስጥ ከ እኔ እና ከ እማዬ ወጪ የሚኖር ሰው የለም የቤታችን ግቢ አነስ ያለና ጠባብ የሚባል አይነት ነው የዛሬን አያርገውና ሙና ይህቺ ጠባብ ግቢያችን ፅድት አድርጋ ትይዘው ስለነበር ሰፊ ግቢ ካላቸው ሰዎች በተሻለ ያምር ነበር ሙኒ አበባ መትከል እነሱን መንከባከብ በጣም ያስደስታታ ነበር በዚች በጠባብ ግቢ ላይ በግራና ቀኝ በጣሳ በጣሳ ተደርገው የተቀመጡ አበባዎች አሉ በእርግጥ አበባዎቹ ለግቢው ውበት ቢሰጡትም በዛ ከተባለ አምስት ሰው ብቻ የማሚያቆም ቦታ ነው ያለው ስለግቢያችን እያወራሁ አደከምኳቹ አይደል እና ካቆምኩበት ልቀጥልና እማዬ የሰራችውን ቁርስ ድብን አድርጌ ከበላሁ በኃላ የበለሀበትን እማዬ እንድታነሳው ትቼላት ተነሳሁ በነገራችን ላይ እማዬ ምንም አይነት ምግብ ብትሰራ ሁሌም ቢሆን እየጣፈጠኝ ጥርግ እድርጌ ነው የምበለው እንዲህ ሲሆን እማዬን ደስ ይላታል ለ ነገሩ ባይላትም እማዬ የሰራችውን ምግብ መተው አያስችለኝም ።

.

ከጓደኞቼ ጋር በጠዋት ለመገናኘት ተነጋግረን ስለነበር ቁርስ ከበላሁ በኃላ ፀጉሬን ወደ ሳሎን ቤት ከመግቢያው በር ጎን በተንጠለጠለው መስታወት ሳየው ቆሽሿል የብርድ ልብስ የተነጫጨጨ ስላለው ጓደኞቼ ጋር ከመሄዴ በፊት ታጥቤ ልፈርዘው ብዬ ወደ መኝታ ቤታችን ገባሁ ....

ሁል ግዜ እኔ የምጠቀምባቸውን እቃዎች በስርአቱ አላስቀምጥም እማዬ ሁል ግዜ ነው የምትቆጣኝ እቃህን በስርአቱ አስቀምጥ እያለች ትናገረኛለች ግን ልምድ ሆኖብኝ ነው መሰል እንድም ቀን በስርአቱ አስቀምጬ አላውቅም ። ዛሬም ጂሌን የት እንዳስቀመጥኩት አላውቅም መኝታ ቤቱን እየዞርኩ ፈለኩኝ ግን አላገኘሁትም ወደ ሳሎን ቤት ሄጄ እማዬን ስጠይቃት እንዳላየችው ነገረችኝ ምን ላድርግ እንዳልተወው ፀጉሬ ቆሽሿል ከታጠብኩ ደግሞ የግድ ጂል መቀባት አለብኝ የኔ ፀጉር ጂል ካልተቀባሁት በጣም ነው የሚያስጠላው ከመፈለግ ውጪ ሌላ ምርጫ ስላልነበረኝ በድጋሚ ለመፈለግ ወደ መኝታ ቤት ገብቼ መፈለጌን ተያያዝኩት አሁንም ላገኘው አልቻልኩም ሁሉም ቦታ ፈልጌ ሳጣው በቃ ልተወው ብዬ ልወጣ የመኝታ ቤቱ በራፍ ላይ ስደርስ ለካ አልጋው ስር አልፈለኩም ብዬ ተመልሼ ወደ ወስጥ ገባሁ በጉልበቴ ተንበርክኬ ከወገቤ ዝቅ ብዬ እጄን ወደ አልጋው ስር ልኬ ጂሌን ስፈልግ እጄ የሆነ በፈስታል የታሰረ እቃ ላይ አረፈ በእጄ ስነካው ትንሽ ጠጠር ያለ ነገር እን መፅሀፍ ነገር ይመስላል ምን እንደሆነ ለማወቅ ስለፈለኩ ፌስታሉን በእጄ እየጎተትኩ ከ አልጋው ስር አወጣሁት ፌስታሉ አቧራ ብቻ ነው አቧራውን በእጄ እንደ ማራገፍ አድረጌ የተቋጠረውን ፌስታል ለመፍታት መታገል ጀመርኩ በጣም ጠብቆ ስለታሰረ በቀላሉ መፍታት አልቻልኩም ታግዬም ቢሆን በመጨረሻ ፈታሁት ፌስታሉ ውስጥ ሁለት መካከለኛ የሆኑ የህይወት ታሪክ መማፊያ (ዲያሪ) ደብተሮች አሉ የማን ነው ብዬ ለመክፈት ስሞክር በቁልፍ ተቆልፎዋል ። መክፈት አልችልም ማለት ነው ግን የሰው ሚስጥር ማየት ምን ያደርግልኛል ብዬ እንደመጀመሪያው ፌስታል ውስጥ ከተትኩት እውነት ለመናገር የማን እንደሆነ ለማወቅ እና ለማየት በጣም ጓጉቻለሁ ግን ተቆልፋል ሲያናድ ቁልፉ ባይኖር ኖሮ አነበው ነበር ቁልፉን ለመስበር ስታገል እማዬ ከመጣች ስለምትቀጣኝ ነው የተውኩት እማዬ ከቤት ስትወጣ እሰብረዋለሁ ብዬ እዛው አልጋው ስር መለስኩት ። አገኝኃው እንዴ አለችኝ እማ ሳሎን ቤት ውስጥ ሆና እኔ ምን እየፈለኩ እንደነበር እራሱ አረስቼዋለሁ ሀሳቤ እንዳለ ፌስታሉ ላይ ስለነበር ምኑን ብላትስ ለእማዬ.....

... አንተ ቀልበ ቢስ ምኑን ትለኛለህ እንዴ ልትፈልገው የገባኸውን ነዋ... ስሙ ምን ነበር ይሄ ለ ፀጉርህ የምትቀባውን ስትለኝ ጀል ልፈልግ እንደ ገባሁ አስታወስኩ እውነትም ቀልበ ቢስ ነኝ..

.

... አንዳላገኘሁት ለእማዬ ነግሪያት መኝታ ቤቱን ለቅቄ ወጣሁ። አማራጭ ስላጣሁ ፀጉሬን በጠር በጠር አድርጌ በትንሽዬ ቅባት ነካክቼ ወጣሁ ጓደኞቼን አግንቼ ትንሽ ካወራን በኃላ እኔ ስለደበረኝ ወደ ቤት ተመለስኩ እንደ አጋጣሚ ሆኖእቤተት ስደርስ እማዬ እቤት አልነበረችም ። ቤቱ አልተስተካከለም እነንዳደርንበት ነበር የእማዬን ያህል ባይሆንም ያቅሜን ያህል እያስተካከልኩ ሳለሁ ያ የቅድሙ ፈስታል አስታወስኩ የማስተካክለውን ቤት ትቼ ወደ መኝታ ቤት አመራሁ ፈስታሉን ካስቀመጥኩበት አንስቼ ወስጡ ያለውን ዲያሪ አወጣሁ ። ቁልፉን ለመክፈት ያስብኩትን ያህል አላስቸገረኝም በቀላሉ ተከፈተልኝ የዲያሪው የመጀመሪያ ገፅ ላይ በትልቁ በ አልበም ሳያዝ የተለጠፈ የወንድ ፎቶ አየሁ ልጁ ለ አይኔ አዲስ አልነበረም ግን የሱ ፎቶ ያለበት ዲያሪ እኛ ቤት ውስጥ ምን ይሰራል ?እያልኩ ቀጣዮን ገፅ ገለፅኩ በቀጣዩ ገፅ በስተ ግራ በኩል ዋሌት ፎቶ ተለጥፎዋል ፎቶው የሙና እና የመጀመሪያ ገፅ ላይ የለው ልጅ አብረው የተነሱት ፎቶ ነው። ሙና ማለት የ አክስቴ ልጅ ናት እኛ ቤት ትኖር ስለነበር አብዛኛው እቃዎቿን እኛ ቤት ነበር የምታስቀምጠው።

ሙና ሁሉም ነገር ሳይበዛ ሳያንስ የተሰጣት ይመስላል ቆንጆ የምትባል አይደለችም ግን አታስጠላም የ ሆነ የሚስብ ነገር አላት ቁመቷ እረጅም አይደለችም አጭርም አትባልም መካከለኛ ቁመት ያላት ናት የፊቷ ከለር ቀይ የሚባል አይደለም ጥቁርም አይደለችም ጠየም ያለች ቸኮሌት ከለር ነገር ነች ።

.

ሙና እኛ ቤት ውስጥ ከ አስር አመት በላይ ኖራለች ።ግን እንዴት ዲያሪ ስትፅፍ አይቻት አላውቅም ? ሙና የአክስቴ ልጅ ትሁን እንጂ ለ እኔ ልክ እንደ እህት ነበረች መወለድ ቋንቋ ነው አይደል የሚባለው .....

ዲያሪውን ማንበብ ፈልጊያለው ግን ትንሽ ከበደኝ የግሏ ሚስጥር ነው ብዬ ዲያሪውን ወደ ነበረበት መልሼ ወደ ፅዳቴ ተመለስኩ እንደ ነገሩ ቤቱን አፀዳድቼ ጨረስኩ ።ያው እንደምታውቁት ግቢያችን መስተካከል የሚያስፈልገው አይነት አይደለም የወዳደቁትን አቃዎችን አነሳስቼ ወደ ሳሎን እንደገባሁ በስተ ግራ በኩል ባለው ከፍ ተደርጎ በተሰራው የ እንጨት ወንበር ላይ ተቀምጬ ትንሿ ስልኬን ከኪሴ አውጥቼ ካንዲ ክረሼን መጫወት ጀመርኩ ግን ቀልቤ እንዳለ ዲያሪው ጋር ነው ቆይ ግን ባነበው ምን ችግር አለው ኧረ ግን የሰውን ሚስጥር ማንበብ ይደብራል እያልኩ ከራሴ ጋር ማውራት ጀመርኩ በመጨረሻም አንድ ውሳኔ ወሰንኩ የ እህቴ አይደል ባነበው ችግር የለውም ብዬ ዲያሪውን ከመኝታ ቤት ወደ ሳሎን ቤት ይዤው መጣሁ በኤል ሼፕ ቅርፅ በተነጠፈው ፍራሽ መሀል ተቀምጬ ማንበብ ጀመርኩ.....

፡

፡ ይቀጥላል

ልብ ወለድ

አንባቢዎች መሪዎች ናቸው!!

https://t.me/amharicfiction

"ያልተፈታ ህልም "

ክፍል 2

✍በሂክማ ጀማል

፡

፡

ንባቤን ከዋሌቱ ፎቶ ትንሽ ወረድ ብሎ ከተፃፈው ፅሁፍ ጀመርኩ ።

ቀኑ ጁምአ (አርብ) ነበር ከሙአዝ ጋር የተዋወቅንበት ቀን ነው ብዙ ግዜ እኔ እና ጓደኞቼ ከምንማርበት ክፍል አጠገብ ተሰብስበን እንቆማለን ብዙ ሆንን ስለሆነ የምንቆመው ከኛ አጠገብ በሚያልፉ ተማሪዎች ላይ ሙድ ለመያዝ ያመቸናል ሙአዝ ከግቢያችን ሙደኛ ከሚባሉት ተማሪዎች ውስጥ አይደለም አለ አይደል የሆነ ፋራ ነገር ይመስላል አለባበሱ ግን ፋራ ነው ለማለት ይቸግራል ። እና እኛ አንደለመድነው ተሰብስበን ቆመን ነበር ሙአዝ ወደ እኛ ኮሪደር የሚያመጣውን ደረጃ ጨርሶ ወደ እኛ መምጣት ጀመረ እኔ ነበር ከሁሉም ቀድሜ ያየሁት ለ ሂወት አሳየኃት ሂወት ማለት ከሌሎቹ በተሻለ የምቀርባት ጓደኛዬ ናት ሚስጠረኛዬም ናት ሂወት እብድ ነገር ናት እኔ እንዳሳየኃት ለሁሉም ኸረ የሚመጣውን ልጅ እዩት አለቻቸው ሰባታችንም በአንድ ላይ ሙአዝ ወደ ሚመጣበት አቅጣጫ ዞርን አስብት አስራ አራት አይን ሁሉ በአንድ ላይ አንድ ሰው ላይ ሲያርፍ .... ራሄል ቀልደኛ ነገር ነች ሼም ምናምን አልፈጠረባትም ሙአዝ ወደ እኛ ሲቀርብ

.... ሪቾ አሁን እንዲ ለብሶ ስታዩት አራዳ ይመስላል ብታናግሩት እኮ አማርኛ እራሱ በስርአቱ መናገር እይችልም ስትል ሁላችንም በአንድ ድምፅ ሀሀሀሀሀሀሀኪኪኪኪኪኪኪ እያልን ኮሊደሩን በሳቅ ቀወጥነው ሙአዝ ከአጠገባችን እየቀፈፈው አለፈ ምን እንዳልነው ቢሰማ ደግሞ ምን እንደሚሆን እንጃ... ሙአዝ ከ እኛ አጠገብ ሲያልፍ አጥፎ ከያዛቸው ሁለት ደብተሮች መሀል እስክሪብቶው ሾልኮ ወደቀ ሪቾ ቀድማ አይታው ስለነበር እዩት ሲደናበር እስክሪብቶውን ጥሎ ሄደ ስትል በድጋሚ ሁላችንም ሀሀሀሀሀ ኪኪኪኪኪኪ ብለን ሳቅን ሙአዝ ጓደኛውን ፈልጎ ነበር የመጣው የሙአዝ ጓደኛ ከኛ ክፍል አጠገብ ያለው ክፍልነው ሙአዝ ጓደኛውን ፈልጎ ስለነበር የመጣው ወደዛው ገባ እኔ እስኪርብቶውን አንስቼ ተቀላቀልካቸው ልስጠው አይደል አልኳቸው ሪቾ እንደ ለመደችው ልታሾፍብኝ እንደሆነ ባውቅም ጠየኳቸው ግን ሁሉም ዝም አሉኝ እ ልስጠው አይደል አልኳቸው በድጋሚ ሪቾ አው ሂጂ ስጭው አለችኝ እኔም እሺ ብዬ ልሰጠው ትንሽ እንደተራመድኩ ሪቾ "የምን እዩኝ እዩኝ ነው ያለመደብሽን ተመለሽ ባክሽ "አለችኝ ተሸማቅቄ ወደ ነበርኩበት ተመለስኩ ሁሉም እየሳቁ ምነው ፋራው ተመቸሽ እንዴ ምናምን እያሉ ሙድ ያዙብኝ ለነገሩ ልክ ናቸው እንኳን የወደቀ አይደለም እየሰረቀ አዛ የሚያደርገው ማን ሆነና ዛሬ ጭራሽ የወደቀውን አንስቼ ልስጠው ለራሴም ገረመኝ

በአላፊ አግዳሚው ላይ ሙድ እየያዝን ትንሽ እንደቆየን የሙአዝ ጓደኛ ወደ እኛ መጣ ራቾ መቼም አፏ አያርፍም ጓደኛው ወደ እኛ ይበልጥ ሲቀርብ "ያ ፋራ እስኪርብቶ ጠፋኝ ብሎ እያለቀሰ ይሆናል አለች "እኛ እንደሆነ መሳቅ ነው ስራችን አሁንም ሀሀሀሀሀሀሀ ኪኪኪኪኪኪኪኪ እያልን የሙአዝ ጓደኛ አጠገባችን ቆሞ ከዚህ ጋር ያነሳችሁት እስኪርብቶ ስጡኝ አለ ሪቾ አላልኳችሁም ስትለን በድጋሚ ሳቅን ጓደኛው ሳቃችን አናደደው

ነኢማ የማን ነው እስክሪብቶው ያንተ ነው አለችው

አይ የጓደኛዬ ነው አላት

... እና እራሱ አይመጣም አለችው ሪቾ ከአፏ ቀበል አድርጋ አይ እሱ ያፍራል አለች ።

ሁላችንም አንድ ላይ ሳቅን ጓደኛው ተናዶ ወደ ክፍሉ ሄደ ብዙም ሳይቆይ ከሙአዝ ጋር ተመለሰ ሪቾ በለመደ አፏ እዩት እዩት አባብሎ አመጣው ስትል ከመጀመሪያው የበለጠ ሳቅን ሀሀሀሀሀሀሀሀሀ ኪኪኪኪኪኪኪኪኪ ለረጅም ሰአት ሙአዝ እየደበረው ወደ እኛ መጣ እስኪርብቶዬ ማን ጋር ነው አለን እኔ ቶሎ ብዬ ይሀው ብዬ እጇን ዘረጋሁ እሱም ሊቀበለኝ አጁን ሲዘረጋ ሂዊ ከ እጇ ላይ መንትፋ ወሰደችው የሙአዝ ጓደኛ አምጭው እንጂ ብሎ ሂዊ ላይ ጮኸባት ነኢማ አንደውም ብላ የእስኪሪበቶውን ከ ሂዊ ተቀብላ ረጋገጠችው ተሰባበረ የሙአዝ ጓደኛ ነኢማን ሊመታት ሰነዘረ አላወቃትም እንጂ ከ እሱ የባሰች ነበረችና እሱ ሲሰነዝር እሷ ከስር ቀረቀረችለት ሄኖክ የሰነዘረውን እጁን ወደ ታች መልሶ በጉልበቱ ተንበርክኮ ወደቀ እኛም ወዲያው ከቦታው ዘወር አልን ነኢማ በድጋሚ ዞራ ወንድ በሆነ እንዳይመስልህ ብላው ከደረጃው ወረድን ።

ቀጣዩን ገፅ ለማንበብ ስገለፅ የውጭ በራችን ተንኳኳ ዲያሪውን የነበረበት ቦታ ላይ አስቀምጬ በር ልከፍት ወጣሁ እማዬ ነበረች በምን አይነት ሰአት መጣሽ እማዬ አልኩ በሆዴ አሁን እንዴት ነው የማነበው ሲያናድ እያልኩ ወደ ሳሎን ገባሁ በራፉ ላይ ባለው የእንጨት ወንበር ላይ ተቀምጬ የፈረደበት ካንዲ ክረሺን ማፍረስ ጀመርኩ ይገርማል ግን ፀባይኛ ፀባይኛ የሚሰራራት ሙኒ እንዲህ ነበረች አንገት ደፊ..... አለ

.... እማዬ ቤቱን ስላፀዳሁላት በጣም ደስ አላት "በረካ ሁን" አለችኝ በነገራችን ላይ እማዬ ምንም ሰርቼላት በረካ ሁን ካላለችኝ ቅር ይለኛል ከልጅነቴ ጀምራ ትለኝ ስለነበር ካላለችኝ በስራዬ ያላስደሰትኳት ይመስለኛል ይሄ በረካ ሁን የሚለው ቃል ለ እኔ እንደ ሽልማት ነው ።።

.... ቀጣዩን ገፅ ለማንበብ በጣም ጓጉቻለሁ ግን እንዴት ብዬ ነው የማነበው እማዬስ?

፡

፡

ይቀጥላል

https://t.me/amharicfiction

"ያልተፈታ ህልም"

ክፍል 3

✍ በሂክማ ጀማል

፡

፡

እኔ ወንበር ላይ እንደተቀመጥኩ ነኝ እማዬ ፍራሹ ላይ ጋደም ብላለች መኝታ ቤት ገብቼ አልጋው ጫፍ ላይ ተቀምጬ ዲያሪውን ገለጥኩት ...

... እኔ የሙአዝ ጓደኛ እያሳዘነኝ ከደረጃው ወረድን ግማሻችን ሶሶት ሆነን ግማሻችን ደግሞ አራት ሆነን ተከፋፍለን ፊት እና ኃላ ሆነን ፎቁን ወርደን ጨረስን የኛ ክፍል አራተኛ ፎቅ ላይ ስለሆነ ወደ ታች ለመውረድ የተወሰነ ሰአት ይፈጃል ከፎቁ ስር የምንቀመጥበት ቦታ አለን ማንም አዛ ቦታላይ አይቀመጥም ።።

የእውነት ግን ለምን መታሸው አለች ሀና

ሀና ከእኛ ትንሽ ትሻላለች ማለት ብዙምሙድ መያዝ ምናምን አይመጥትም

ነኢማ ፡- ኧረ አይ እኔን እስኪመታኝ አጠብቀዋለሁ አለች

እኔ ከተቀመጥንበት ቦታ ተነስቼ ወደ ፎቁ ወጣሁ ወዴት ነው አለችኝ ሪቾ ክላስ ደርሼ ልምጣ አልኳት

ምነው ልታባብይው ነው አለችኝ ሪቾ ሁሉም ሳቁብኝ ግን አልተመለስኩም ወደ ክፍል ገብቼ ከሰረኳቸው እስኪርብቶዎች አንዱን ይዤ ወጣሁ ሙአዝ እና ጓደኛው እዛው የቆሙበት ቦታ ላይ ነበሩ እስኪርብቶውን ለሙአዝ ሰጠሁት ይቅርታ እሺ እኛ ለጨዋታ ብለን ነው የሙአዝ ጓደኛ ኧረ እንዲህ በቀላሉ አለ ሙአዝ ይቅርታ አለችህ አይደል ብሎ እስኪራብቶውን ተቀብሎኝ እሺ በቃ ችግር የለውም አለኝ።።

አሺ ብዬ ከደረጃው ሰወርድ ሙአዝ አጠገቤ መጥቶ አልተዋወቅንም እኮ ብሎ እጁን ዘረጋልኝ እኔም የዘረጋውን እጁን ጨብጬ ሙና እባላለሁ አልኩት ሙአዝ እንደሚባል ነገረኝ ትንሽ ከቆየሁ እነ ሪቾ ስለሚመጡ የጨበጥኩትን እጅ ለቅቄ ሰወርድ የሙአዝ ጓደኛ እኔ

ግን አልሰማቹም እሺ አለኝ ምንም ሳልመልስለት ሄድኩ ደረጃውን ወርጄ እነ ሪቾን ተቀላቀልኳቸው እ እንዴት በዚህ ፍጥነት ዝም አስባልሽው አለችኝ ሪቾ

 የምር ግን አይተውኝ ከሆነ ነቆራቸውን አልችለውም እኔም ለማስቀየስ ብዬ ምን ሆነሽ ነው ልጅቷ እኮ እኔ ነኝ አልኳት እንዲሁ የማይረባ ወሬ እያወራን ትንሽ እንደቆየን ሙአዝና አሙአዝ ጓደኛ ደረጃውን ወርደው ጨርሰው ወደ እኛ መጡ እንዴት እንደደነገጥኩ ያደረኩትን ነገር መጥተው እንዳይዘባርቁ ፈርቻለሁ የሙአዝ ጓደኛ እንዳሰብኩት ይቅርታ ስላልሽ ብቻ የምንላቀቅ እንዳይመስልሽ ብሎን አለፈ ሪቾ ማን ይቅርታ አለህ እንደውም አንተ እራስህ ይቅርታ ካላልክ አንላቀቅም አለችው ምን ልበል አንገቴን አቀርቅሬ ዝም አልኩ ዊንታና ነገረ ቶሎ ነው የሚገባት እና ማን ነው ሄዶ ይቅርታ ያለቸው አለች እኔ እያየቸ ሁሉም እኔ ላይ አፈጠጡ በቃ መደበቅ ስላልቻልኩ እኔ ነኝ ያልኳቸው ሪቾ አበደችብኝ እንዴት ይቅርታ ትይዋለሽ አሰደብሽን ብላ ከተቀመጠችበት ተነስታ ሄደች እኔም ተከተልኳት እነ ሙአዝ ብዙም አራቁንም ነበር ጠርታ አስቆመቻቸው "ስማ ስማ ማንም ይቅርታ አላለህም እሺ እሷ በራሷ ነው ያለችህ ይቅርታ የተባልክ መስሎህ እንዳትንጠባረር "ብላው መልስ ሳትጠብቅ ሄደች እኔም እዛው ቆምኩ እነ ሙአዝም ሄዱ ።።

ቆይ ምን መሆኔ ነው ነው ለምንድን ነው እንዲህ የማደርገው ሂዊ መጥታ እዚህ ምን ታደርጊለሽ ነይ እንጂ ብላኝ ወደ ምንቀመጥበት ቦታ ሄድን ሁሉም ዝም ብለዋል ይጨንቃል ዊንታና ከእኛ የኑሮ ሁኔታ ሻል ያለ ኑሮ ነው የምትኖረው የመንግስት ትምህርት ቤትም የገባችው ኤልዳናን ፊልጋ ነው ኤልዳናና ዊንታና ከ አራተኛ ክፍል ጀምሮ ጓደኞች ናቸው አሁን ወደ ዘጠነኛ ክፍል ሲያልፉም ላለመለያየት ብለው ነው አንድ ትምህረት ቤት የገቡት ዊንታና ስልኳን አውጥታ የሳያት "አሁንም አሁንም እተነፍሳለሁ ትምህርት አልገባኝም ዝም ብዬ ሰራለሁ..." የሚለውን ዘፈን ከፍታ ዝምታውን ሰበረችው ሪቾ ይሄን ዘፈን በጣም ትወደው ስለነበር ከዘፈኑ እኩል እያለች መጮህ ጀመረች.....

፡

፡

 ይቀጥላል

ልብ ወለድ

አንባቢዎች መሪዎች ናቸው!!

https://t.me/amharicfiction

"ያልተፈታ ህልም"

ክፍል 4

✍ በሂክማ ጀማል

፡

፡

..... ዘፈኑ እንዳለቀ ተደወለ የምሳ ሰአት ስለነበር ምሳ አልበላንም ነበር ሁሌም ምሳ የምንበላው ወደ ክፍል እንድንገባ የሚያሳውቀን ደውል ሲደወል ነው ከተደወለ በኃላ ነው ከፎቁ ጀርባ ሄደን በሽሚያ የምንበላው ምሳ በልተን ወደ ክፍል ስንሄድ አስተማሪ ገብቶ ነበር በሰአቱ የገባው አስተማሪ አጉል ወግ አጥባቂ ነገር ነበር እረፍዶዋል አትገብም አለን ምንም ሳንናገር እዛው ቆምን በሩን እላይላያችን ላይ ዘግቶ ገባ እኛም እንደለመደብን ኮሊደሩ ላይ ተደርድረን ቆምን አምስታችን ብቻ ነበር ምሳ የያዝነው ሄለን እና ሪቾ አልያዙም ነበር የምሳ

እቃችንን ደራርበን በ አንድ በኩል አስቀመጥነው ተከፋፍለን የየገል ወሬያችንን እያወራን ሳለን የክፍላችን በር ተከፈተ ሁላችንም ወደ በሩ ዞርን መምህሩ ነበር ለዛሬ ግቡ እንዳይደገም አለን ሂዊ የሁላችንንም ምሳ እቃ ይዛ ገባን የምንቀመጠው አንድ ላይ ነው አንድ መደዳ ላይ አምስት ረድፎች አሉ ከኃላ ጀምሮ ያሉት ሶስት መቀመጫዎች ላይ ነው የምንቀመጠው በየ ቦታችን ተቀመጥን ከኛ ፊት ያሉ አራት ተማሪዎች አሉ ሁሌ የሚገርመኝ ነገር ቢኖር እኔ የቡድን መሪ መደረጌ ነው ትምህርት ቤት የምመጣው ለመማር ሳይሆን አዛ ለማድረግ ነው ለነገሩ ሁላችንም አንድ አይነት ነን በነገራችን ላይ የኛ ቡድን የራሳችን የሆነ ህግ አለን ማናችንም ብንሆን ከማንኛውም አይነት ወንድ ጋር የፍቅር ግንኙነት መጀመር አንችልም ከጀመርን ከቡድን አንገለላለን እኛ በራሳችን መንገድ ፈታግለት ነው ሙዳችን ወደ ክፍል ገብተን ብዙም ሳንቆይ የቀጣዩ ክፍለግዜ ተደወለ የእስፖርት ክፍለ ግዜ ስለነበር ሁላችንም ቀያይረን ወጣን የሚገርመው እነ ሙአዝም ወጥተው ነበር ሪኞ ገላምጣቸው አለፍን ክፍለ ግዜው ሲያልቅ ሙአዝ እና ጓደኛው ወደ እኛ መጥተው ለሪኞ በቃ ፒስ እንፍጠር አላት ትንሽ እንደ ማንገራገር ብላ ተስማማች ደስ አለኝ ለምን ደስ እንዳለኝ ግን አላውቅም ሙአዝን ፈገግ ብዬ ተመለከትኩት የዛሬን ቀን እንዲህ አሳልፈን ወደ የቤታችን ሄድን በነጋታው ወደ ትምህርት ቤት ለመሄድ ከሰፈር ስወጣ ሙአዝን እኛ ሰፈር አገኘሁት እሱ አላየኝም ነበር ጠርቼ አስቆምኩት ደስ የሚል ፈገግታ ፊቱ ላይ ይታያል ሰላም ለማለት እጄን ስዘረጋለት ወደ እራሱ ስቦ አቀፈኝ እሱም ወደ ትምህርት ቤት እየሄደ ስለነበር አብረን ሄድን ወደ ትምህርት ቤት እየሄድን ስለተለያዩ ነገሮች አወራን ስለ ቡድናችንም ነገርኩት ደስ ይላል ግን ለምን የፍቅር ግንኙነት መመስረት ተከለከለ አለኝ በቃ እንዲሁ ሌላ ሙድ ውስጥ እንዳንገባ ብለን ነው አልኩት ትምህርት ቤት በራፍ ላይ ሪኞን አገኘናት እሷ እንደሆነ አፏ አያርፍም ኧረ እዩልኝ እያለች ወደ እኛ መጣች እኔን ስማኝ ሙአዝን ጨበጠችው ስማ ባክህ ከ እቤቷ አስጠርተህ ነወ አይደል ያመጣህት አለችው ሙአዝ ፈገግ ብሎ ዝም አላት ወደ ግቢ ገብተን የምንሰበሰብበት ቦታ ላይ ስንደርስ ሁሉም መጥተዋል ሶስታችንም ሰላም ብለናቸው ተቀላቀልናቸው ሙአዝ በቃ እኔ ልሂድ አለ ሪኞ ምነው ደበርንህ እንዴ አለችው ኧረ አልደበረኝም ጓደኞቼ ከመጡ ልያቸው ብዬ ነው እሺ በቃ ሂድ አለችው ሙአዝ ፎቁን ሲወጣ እኔም በአይኔ እየተከተልኩት አብሬው ወጣሁ ኧረ ንቀይ እነጂ ልትስይው ነው እንዴ አለችኝ ሪኞ ግን ለምን አይቀላቀሉንም አለች ሂዊ እኔ አዎ ለምን አይቀላቀሉንም አልኩ ይቻላል በቃ እንነግራቸዋለን ተባብለን ወደ ክፍል ገባን የ እረፍት ሰአት ተደውሎ ወጣን እንደተለመደው ኮሊደሩ ላይ ቆምን ሙአዝ ሄኖክን ፈልጎ መጣ ከ አጠገባችን ሲያልፈ ዊንታና ጠራችው ወደ እኛ መጣ ሂዊ እንዲቀላቀሉን ጠየቀችው ሙአዝ እየፈገገ ፊቃደኝነቱን ነገራቸው አና ሊሄድ ሲል ኤልዳና ስማ ስማ ሀጉን ግን ታከብራላቹ እሺ አለችው የምን ህግ ነው አለ ሪኞ ከ እኛ ጋር ከሆንክ ምንም ነገር ቢሆን መደባበቅ አይቻልም ለየ ግል መሆን አይቻልም እና ከ ቡድኑም ሆነ ከቡድኑ ውጪ ከሆነ ሰው ጋር የፍቅር ግንኙነት መጀመር አይቻለም አለችው ተስማምቻለሁ ብሏት ሄደ ሙአዝ ለጓደኛው ነገረው እሱም ተስማምቶ አብረን መዋል ጀመረን .....

፡

፡

ይቀጥላል

ልብ ወለድ

አንባቢዎች መሪዎች ናቸው!!

https://t.me/amharicfiction